# የተሰጠን፡ መንፈስ - ኃይል

እግዚአብሔር፡ የሰጠን፡ የኃይል፣ የፍቅርና፡ ራስን፡ የመግዛት፡ መንፈስ፡ እንጂ፡ የፍረሃት፡ መንፈስ፡ አይደለም። እንኝህን፡ ሃሳቦች፡ በየተራ፡ እንመለከታለን። በመጀመሪያ፡ እዚህ፡ ስፍራ፡ ላይ፡ እንደተመለከተው፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ የኃይል፡ መንፈስ፡ እንደሆነ፡ ነው። የእግዚአብሔር፡ ቃል፡ "መንፈስ፡ ቅዱስ፡ በናንተ፡ ላይ፡ በወረደ፡ ጊዜ፡ ኃይልን፡ ትቀበላላችሁ" ይላል (ሐዋ 1፡ 8)። ይህ፡ ኃይል፡ ለአገልግሎት፡ የሚያቆም፡ ኃይል፡ ነው። ይህ፡ ኃይል፡ ድንቅና፡ ታምራትን፡ የሚያደርግ፡ ኃይል፡ ነው። ይህ፡ ኃይል፡ መገለጥን፡ የሚያመጣ፡ ነው። ለዚህ፡ ነው፡ ለመጀመሪያዎቹ፡ አማኞች፡ ኃይልን፡ ከተቀበሉ፡ በኃላ፡ የክርስቶስን፡ ወንጌል፡ ከአካባቢያቸው፡ ጀምረው፡ በምድር፡ ሁሉ፡ ትመሰክራላችሁ፡ የተባሉት።

መንፈሳዊ፡ አገልግሎትን፡ ለመፈጸም፡ የምንችለው፡ በውስጣችን፡ በሚሰራው፡ የእግዚአብሔር፡ መንፈስ፡ ልክ፡ ነው። የጌታ፡ ኢየሱስ፡ አገልግሎት፡ የመንፈስ፡ ቅዱስ፡ አገልግሎት፡ ነበር። ጌታ፡ ከአብ፡ ጋራ፡ ሕብረት፡ እንደነበረው፤ ከመንፈስ፡ ቅዱስም፡ ጋርም፡ አስደናቂ፡ የሆነ፡ ሕብረት፡ ነበረው። በዮርዳኖስ፡ ሲጠመቅ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ በእርግብ፡ አምሳል፡ ሆኖ፡ ወርዶበታል። ጌታ፡ መንፈስ፡ ቅዱስን፡ አጽናኙ፡ ይለዋል። ወደ፡ እውነት፡ የሚመራ፡ ይለዋል። ስለ፡ አብና፡ ወልድ፡ የሚመሰክር፡ ይለዋል። ከመንፈስ፡ ቅዱስም፡ ጋር፡ ካለው፡ ሕብረት፡ የተነሳ፡ አገልግሎቱ፡ በኃይል፡ የተሞላ፡ ነበር። መጽሓፍ፡ ስለዚህ፡ ጉዳይ፡ ሲናገር፡ "እግዚአብሔር፡ የናዝሬቱን፡ ኢየሱስን፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ በኃይልም፡ ቀባው፥ እርሱም፡ መልካም፡ እያደረገ፡ ለዲያብሎስም፡ የተገዙትን፡ ሁሉ፡ እየፈወሰ፡ ዞረ" ይለናል (ሐዋ 11፡ 38)። ሐዋሪያው፡ ጴጥሮስም፡ በበአለ፡ አምሳ፡ ቀን፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ በኃይል፡ ከወረደበት፡ በኋላ፡ አገልግሎቱ፡ በአስደናቂ፡ ሁኔታ፡ እንደተለወጠ፡ እናስተውላለን። ፈሪ፡ የነበረው፡ ሰው፡ የክርስቶስን፡ ወንጌል፡ በታላቅ፡ ኃይል፡ በመስበክ፡ ብዙዎችን፡ ወደ፡ እውነት፡ ሲመልስ፡ እናያለን። ያልተማረና፡ አሳ፡ አጥማጅ፡ የነበረው፡ ጴጥሮስ፡ የነቢያትን፡ መጽሓፍት፡ ሲገልጥና፡ ሲተነትን፡ እናያለን። ብዙ፡ ድንቆችና፡ መንፈሳዊ፡ ጥበብ፡ ሁሉ፡ ተራ፡ በነበረው፡ ሰው፡ ሲገለጡ፡ እንመለከታለን። ይህንን፡ ያደረገው፡ በእርሱ፡ ውስጥ፡ የሰራው፡ የእግዚአብሔር፡ መንፈስ፡ ነው።

ክርስቶስ፡ ኢየሱስ፡ የመሰረታት፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ የገሃነብ፡ ደጆች፡ የማይችሏት፡ ናት። የገሃነብ፡ ደጆች፡ የክፋውን፡ የመጨረሻ፡ ጉልበት፡ የሚወክሉ፡ የሞት፡ በሮች፡ ናቸው። ነገር፡ ግን፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ በጌታ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ስትቀባ፡ በገሃንም፡ ደጆች፡ ላይ፡ በማየል፡ የህይወትን፡ ቃል፡ ታበስራለች። ለታሰሩት፡ መፈታትን፤ ለእውሮች፡ ማየትን፡ ትሰብካለች። የተጠቁትን፡ ነጻ፡ ታወጣለች። የክርስቶስ፡ ወንጌል፡ በኃይልና፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ በብዙ፡ መረዳትም፡ እንጂ፡ በቃል፡ ብቻ፡ ወደኛ፡ የደረሰ፡ አይደለም (1ተሰ 1:5)።

ወገኖቼ፡ ቤተ፡ ክርስቲይን፡ እኛ፡ ነን። የእግዚአብሔር፡ አላማ፡ ከመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ጋር፡ ሕብረት፡ በማድረግ፡ የጥላቶቻችንን፡ ደጅ፡ በኃይል፡ እንድንወርስ፡ ነው። ነገር፡ ግን፡ ያለ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ኃይል፡ ምንም፡ ነገር፡ ልናደርግ፡ አንችልም። እንዴት፡ መጸለይ፡ እንደሚገባን፡ እንኳን፡ የሚይስተምረን፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ነው። የእግዚአብሔር፡ ቃል፡ እንግዲህ፡ በጌታና፡ በኃይሉ፡ ችሎት፡ የበረታችሁ፡ ሁኑ፡ እንደሚል፡ ልንበረታ፡ የምንችለው፡ በውስጣችን፡ በሚሰራው፡ የጌታ፡ ኃይል፡ ልክ፡ ነው። ይህ፡ ደግሞ፡ ከርሱ፡ ጋር፡ ባለን፡ ህብረት፡ የሚወሰን፡ ነው። ስለዚህ፡ ይህ፡ የኃይል፡ ጌታ፡ ሁልጊዜ፡ በሕይወታችን፡ እና፡ በአገልግሎታችን፡ እንዲገለጥ፡ ከእርሱ፡ ጋር፡ ያለንን፡ ሕብረት፡ እናሳድግ። ያን፡ ጊዜ፡ የእግዚአብሔር፡ እጅ፡ ስትንቀሳቀስ፡ እናያለን። አሜን!